**<u>አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ</u>**

**<u>የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና ቤንሺ.አ.ኢ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን በመጠቀም የሕብረተሰብ ጤና ምርምርን ለማሻሻል የ3 አመት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።</u>**

ኢትዮጵያ/ ስቴን /ጥር 2 2014 የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት (ኢ.ሕ.ጤ.ኢ) እና ቤንሺ.ኤ.ኣይ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስንና ማሽን ለርኒንግት በመጠቀም በኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ምርምር ውጤቶችን ለማጐልበት የ3 ዓመት የመግባቢያ ሠነድ በዛሬው ዕለት መፈራረማቸውን በጋራ ይፋ አድርገዋል።
መግባቢያ ሰነዱ የሚከተሉትን ሠፋፊ የቅንጅት ስራዎችን ያጠቃልላል።

- **ለአትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ተመራማሪዎች በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዙሩያ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፡** በመጀመሪያ ምዕራፍ ለአንድ ሳምንት የሚቆይ በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስና ማሽን ለርኒንግ ላይ ያተኮረ የመግቢያ ስልጠና ለኢ.ሕ.ጤ.ኢ አስተዳደር፣ ከ50 በላይ ለሚሆኑ ተመራማሪዎችና የጤና ባለሙያዎች ቤንሺ.ኤ.ኣይ ይሰጣል።
- **በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መሳሪያዎች የታገዘ ምርምርና** መረጃን የማጠናከር ስራ በተመረጡ የህብረተሰብ አመጋገብ ስርዓቶች ላይ ማከናወን
- በኢትዮጵያ ጥራታቸውን የጠበቁ የስነ-ምግብ ምርምሮችን ለመስራት **የዚህ የቅንጅት ስራ ውጤቶችን ይፋ ማድረግና** አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን እንዲጠቀሙ ማበረታታት

የኢ.ሕ.ጤ.ኢ የምግብ እና የስነ ምግብ ምርምር ዳይሬክቶሬት ከቤንሺ.ኤ.ኣይ ጋር አብሮ በመሆን ይህን ስምምነት ይመራል። በመሆኑም ከዋና ዋና የምርምር ስራዎች ውስጥ አንዱ የአመጋገብ ተግዳሮቶችና የምግብ እጥረት ችግር ላይ ያተኮረ ነው።

የአርቴፍሽያል ኢንተለጀንስ በሀገር አቀፍ በምግብ እና ስነ ምግብ ምርምሮች ላይ ሲተገበር ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። በቢል እና ሚሊንዳ ጌት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ለትርፍ ያልተቋቋመው ቤንሺ.ኤ.ኣይ ጋር በመስራት የኢ.ሕ.ጤ.ኢ የተሻለ ቴክኖሎጂን እና አሰራሮችን በመጠቀም መረጃ መሰረት ያደረገ ግንዛቤዎችን እንዲሁም ስትራቴጂዎችን በማጐልበት የሕብረተሰብ ጤናን ለማሻሻል ያለመ ነው።

**የምግብ እና የሥነ ምግብ ምርምር ዳይሬክተር የሆኑት ዶክተር ማስረሻ ተሰማ እንደተናገሩት** "ማሽን ለርኒንግ ምርምርን ለማሳደግ ቁልፍ ሚና አለው። የኢ.ሕ.ጤ.ኢ ከቤንሺ.ኤ.ኣይ ጋር አብሮ መስራት የስነ ምግብ ምርምርን በአርቴፍሽያል ኢንተለጀንስ እና በማሽን ለርኒንግ ለማሳደግ ትልቅ ሚና አለው። የማሽን ለርኒንግ እና አርቴፍሽያል ኢንተለጀንስን መጠቀም ለስነ-ምግብ ምርምር ተመራማሪዎች ጥራቱን የጠበቀ የምርምር ውጤቶችን ለማዘጋጀት ይጠቅማል። እንዲሁም ተመራማሪዎች የማሽን ለርኒንግን በመጠቀም ጥራት ያለው የምርምር ውጤቶችን እንዲሰሩ ይህ የጋራ ስምምነት ይጠቅማል። በኢ.ሕ.ጤ.ኢ እና ቤንሺ.ኤ.ኣይ. የተደረገው ስምምነት ከ2022 እስከ 2024 የሚዘልቅ ይሆናል።"

**የቤንሺ.ኤ.ኣይ. መስራች እና ዋና ዳሬክተር የሆኑት ዶ/ር አፍሪካ ፔሬንዝ** የሚከተለውን ብለዋል "ከኢ.ሕ.ጤ.ኢ ጋር አብረን የመስራት ትልቅ እድል በማግኘታችን እጅግ ደስተኞች ነን። የመንግስት ተቋሞች ጋር አብረን መስራታችን የአለም ጤና በማሻሻል ረገድ ቁልፍ ምሶሶ ነው። የእኛን የአርቴፍሽያል ኢንተለጀንስ ባለሞያዎች ከኢ.ሕ.ጤ.ኢ ተመራማሪዎች ተጨባጭ እውቀት ጋር

በማቀናጀት አዲስ መረጃ ላይ የተመሰረተ ለግለሰቦች ለማህበረሰብ እንዲሁም በሕብረትሰብ ጤና ዙሪያ ላይ አዳዲስ ግንዛቤዎችን ወደፊት እናመጣለን።"

ለመገናኛ ብዙሃን እና ሌሎች ጥያቄዎች ካላችሁ ከታች የተጠቀሱትን አድራሻ ተጠቀሙ

ለኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
ምግብ እና ስነ ምግብ ምርምር ዳይሬክቶሬት
ሀሲና ኡስማን (የኮሚኒኬሽን ባለሞያ)
ቤዛ ተሾመ (ዳታ ማናጀር)
Hassina.nipn@gmail.com/beza,nipn@gmail.com
---------------------------------------------------------------------------
ቤንሺ.ኤ.ኣይ
ሱሚኮ ታናካ ፑሽ፣
አለምአቀፍ የአጋርነት መሪ
sumiko@benshi.ai

ስለ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት

የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በጤና ሚኒስቴር የጤና ምርምር ክንፍ ሲሆን የተቋቋመውም የአጠቃላይ ሕብረተሰብ ጤናን ለማሻሻል ፤ ቅድሚያ በሚሰጣቸው የጤናና የሥነ-ምግብ ጉዳዮች ላይ ምርምር በማካሄድ የተጨባጭ መረጃ ተጠቃሚነትንና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ዕውን በማድረግ፣ ውጤታ የሕብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥርን በመተግበር፣ ጥራት ያለው የላበራቶሪ ስርዓት በመዘርጋት እና የህብረተሰብ ጤና ተመራማሪዎችንና ባለሙያዎችን በማሰልጠን ጥራት ያለው የጤና ትግበራ ተደራሽ በማድረግ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ ጤና ማሻሻል ነው። የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትራእይ በአፍሪካ በሕብረተሰብ ጤና የልህቀት ማዕከል መሆን ነው።

ስለ ቤንሺ.አ.ኣይ

ቤንሺ.አ.ኣይ የተባለው ትርፋማ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን በቢል እና ሚሊንዳ ጌት ፋውንዴሽን የገንዘብ እርዳታ የተቋቋመ ሲሆን አላማውም ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ውስጥ የግለሰብን ጤና ለማሻሻል ነው። ለዚያ ዓላማ፤ ቤንሺ.አ.ኣይ ግላዊ፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ግንዛቤን ለህክምና ቡድን እና ለግለሰብ ታካሚዎች ያቀርባል።ድርጅቱ ከታች በተጠቀሱት በአራት ዋና የምርምር ዘርፎች ላይ አተኩሮ ይሰራል።

1. ትምህርትን ማጠናከር (Reinforcement learning)
2. በምክንያታዊ ውሳኔ (Causal inference)
3. ንድፍ ሙከራ (Experimental design)
4. ጠንካራ የትንበያ ሞዴሊንግ (Dynamic predictive modeling)